QUICKNOTES mcps

**ኦክቶበር 31/2018 QuickNotes**

**የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ሱፐር ኢንተንደንት ስሚዝ/MCPS Superintendent Smith የ2020 የበጀት አመት ካፒታል በጀት እና የCIP /ካፒታል ኢንቨስትመንት ፕሮግራም ማሻሻያ አቅርበዋል፤ ለአዲሱ የክላርክስበርግ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት የክልል/ድንበር አስተያየት/ሃሳብ ሰጥተዋል**

ሱፐርኢንተንደንት ጃክ አር. ስሚዝ/Superintendent Jack R. Smith ከዚህ ቀደም በፀደቀው 2019-2024 የካፒታል ማሻሻያዎች ፕሮግራም በጀት ላይ መጠነኛ ማሻሻያ በማድረግ ጠይቀዋል /(FY) 2019-2024 Capital Improvements Program እየጨመረ የመጣውን የተማሪዎች ቁጥር፣ የት/ቤቶች ሠላም/ደህንነት ማስጠበቅ፣ እና ለኮሌጅ እና የሥራ ዝግጁነት ፕሮግራሞችን ለማስተናገድ ።

$1.815 billion/ቢሊዮን የቀረበው አስተያየት ከፀደቀው የስድስት-ዓመት CIP የ $37.6 million/ሚሊዮን ጭማሪ ነው። ለበጀት ዓመት FY 2020 የቀረበው የተሻሻለው CIP $324.33 ሚሊዮን ቀደም ሲል ፀድቆ ከነበረው በጀት የ$15.97 ሚሊዮን ዶላር ተጨማሪ አለው
ለበጀት ዓመት-FY 2020 ወጪ የተያዘ $308.36 ሚሊዮን።

**የት/ቤት የምዝገባ እድገት በአግባብ መያዝ/መምራት/ማስተዳደር**

ለ 2018-2019 የትምህርት አመት የመጀመሪያ ምዝገባ 163,123 ነው፣ ከ 2017-2018 የትምህርት ዓመት በ1,577 ተማሪዎች ጭማሪ ማለት ነው። ከ 2009-2010 የትምህርት ዓመት ወዲህ፣ የ MCPS ትምህርት የሚገቡ ተማሪዎች በ 21,346 ጨምሯል። 2024-2025 የትምህርት ዓመት በ MCPS ትምህርት የሚገቡ ትንበያ 11,199 ተማሪዎችን በመጨመር 174,322 ተማሪዎች እንደሚሆን ነው።

ይህን እድገት ለማስተናገድ፣ በሐይላንድ ቪው/Highland View፣ በሌክ ሴኔካ/Lake Seneca እና በሰርጉድ ማርሻል/Thurgood Marshall አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች ላይ ተጨማሪ የመሥራት እቅድ/ፕላን CIP ማካተት አለበት። እነዚህ ፕሮጀክቶች በካፒታል የማሻሻያ ፕሮግራም ላይ ከተገለጹት ተጨማሪ ናቸው።

**የት/ቤት ሠላም-ደህንነት ማጠናከር**

የሁሉም ተማሪዎች እና ሠራተኞች ደህንነት በ MCPS ቅድሚያ የሚሰጠው ከፍተኛ ትኩረት ነው። የት/ቤቶችን ሠላም/ደህንነት የመጠበቅ አቅም ለማጠናከር፣ አሁን ባሉት የተለያዩ የሰኩሪቲ ሲስተሞች ቴክኖሎጂ ለማዘመን እና በአሁን ወቅት ይህ አይነት ፊቸር የሌላቸውን ደህንነታቸው የተጠበቀ ወደ ውስጥ መግቢያ ቦታዎችን እና ጎብኚዎች ወደ ት/ቤቶች ህንፃዎቹ በምሪት የሚገቡበት ተጨማሪ ገንዘብ/ፈንድ ሱፐርኢንተንደንት ስሚዝ/Superintendent Smith $28 million/ሚሊዮን ተጨማሪ አቅርበዋል።

**ለሥራ ዝግጁነት ፕሮግራሞች ተደራሽነትን ማስፋፋት**

ተማሪዎች በካውንቲው ውስጥ በየትኛውም ቦታ ቢኖሩም ለሥራ ዝግጁነት ፕሮግራሞችን ማግኘት እንዲችሉ ለማድረግ MCPS ቁርጠኛ ነው። በሲልቨርስፐሪንግ የሚገኘው የቶማስ ኤድሰን የቴክኖሎጂ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Thomas Edison High School of Technology) በአሁኑ ወቅት የካውንቲው ብቸኛ ዋና ማዕከል ሆኖ የሚያገለግል ሲሆን የአፐካውንቲ ተማሪዎች ለመድረስ ይከብዳቸዋል። ለአፐካውንቲ/upcounty የሥራ ፕሮግራሞች የበለጠ መዳረሻ ለማግኘት እንዲችሉ ለማድረግ፣ ፋሲሊቲው ለአፐካውንቲ/upcounty የሥራ ፕሮግራሞች ማእከል ሆኖ እንዲያገለግል ለሴኔካ ቫሊ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት/Seneca Valley High School የማጠናከሪያ/ማስፋፊያ ፕሮጀክት ሱፐርኢንተንደንት ስሚዝ/Superintendent Smith የተጨማሪ ገንዘብ/ባጀት አስተያየት አቅርበዋል።

[የዜና መግለጫውን ያንብቡ]

**የዊንተር ኮት/ካፖርት ዘመቻ ተጀምሯል**

የቅድመ ሙዋእለህፃናት እና ቀደምት ጀማሪ ህፃናት ፕሮግራሞች ለተማሪዎች አዳዲስ የክረምት ልብሶችን ለመስጠት እርዳታ እየጠየቁ ነው።

ለወንዶች እና ለሴቶች ልጆች ልክ የሚሆናቸው 5፣ 6፣ እና 7 ቁጥር ኮት (ጃኬቶች) እና ሌሎችም የዊንተር ኮፍያዎች እና የእጅ ጓንቶችን እየሰበሰቡ ናቸው። የገንዘብ እርዳታም ይቀበላሉ። እርዳታው የሚላከው በሚከተለው አድራሻ ነው፡- Rocking Horse Road Center, 4910 Macon Road, Room 141, Rockville, MD 20852.

ለተጨማሪ መረጃ Lisa Conlon በስልክ ቁጥር 240-740-4530 መጠየቅ ይችላሉ።

**የ MCPS ቤተሰቦች ለሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ኢንጅነሪንግ እና ሂሳብ (STEM) ትእይንት ተጋብዘዋል**

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ እና የትምህርት አጋሮቹ የአንደኛ ደረጃ፣ የመካከለኛ እና የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ኢንጅነሪንግ፣ እና ሒሳብ እድሎችን በተግባር እየተሠሩ የሚታዩ እንቅስቃሴዎችን/STEM Festival Showcase ቅዳሜ ኖቬምበር 10 ትርኢት ያቀርባል። ትርኢቱ በኖርዝውድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት/High School, 919 University Blvd ከ 10 a.m. እስከ 2 p.m ይካሄዳል። West, Silver Spring. ይህ ቤተሰብ-አቀፍ የሆነው ትእይንት ለህዝብ ክፍት የተደረገው በነፃ ነው።

ይህ STEM ፌስቲቫል [የሜሪላንድ ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ኢንጅነሪንግ፣ ሒሳብ ፌስቲቫል/Maryland STEM Festival አካል ሲሆን]፣ ከኦክቶበር 26 እስከ ኖቬምበር 11 ይካሄዳል። የሜሪላንድ STEM ፌስቲቫል ቀጣዩን የ STEM መሪዎች/ተወዳዳሪዎች ትውልድ ለማነቃቃት ይፈልጋል።

**የ MCPS ፋውንዴሽን "Dine With Dignity" የተሰኘ ዘመቻ ተጀምሯል**

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ኢጁኬሽናል ፋውንዴሽን/Montgomery County Public Schools Educational Foundation በት/ቤት በመመገቢያ ክፍል የተማሪዎችን ክብራቸውን የመጠበቅ ድጋፍ ለመስጠት ኦክቶበር 29 "Dine with Dignity" የተሰኘ ዘመቻ ያካሄዳል።

ባለፈው ዓመት በ MCPS፣ 34,000 መደበኛ የት/ቤት ምሳ በአማራጭ ምግቦች ተቀይረው ለነፃ የምሣ ፕሮግራም ብቁ ላልሆኑ እና በምሳ አካውንታቸው ላይ $10 ወይም ከዚያ የበለጠ ጉድለት የሚታይ ተማሪዎች ተለዋጭ ምግብ ተሰጥቷል። አማራጩ ምግብ ያስፈለገው ከእኩዮቻቸው እኩል ምሣ ገዝተው ለመብላት የገንዘብ አቅም የማይኖራቸው ተማሪዎችን እየጨመረ የሚሄደውን የማፈር ሁኔታ በመለየት ነው።

በአንፃሩ፣ ዲስትሪክቱ ያልተከፈሉ የሂሳብ ሚዛኖችን ክፍሎ እንዲጨርስና ያልተከፈለ ሂሳብ ያለባቸው ተማሪዎች መደበኛውን የምሣ ምርጫ እንዲደሰቱ ለመርዳት ፋውንዴሽኑ ፈንድ መሥርቷል። የሆነ ሆኖ ቤተሰቦች ከፍለው እንዲጨርሱ፣ ወይም በልጃቸው የምሳ አካውንት ላይ ያልተጠናቀቀ ሂሳባቸውን ቤተሰብ በገቢያቸው ልክ እንዲከፍሉና Dine with Dignity Fund የተቀረውን እንዲሸፍን ይጠየቃሉ።

ይህንን የሚመስል ልዩ የሆነ የልጅነት ረሃብ ግንዛቤ ለማስጨበጥ እና ስለ ዘመቻውም ለማስገንዘብ ፋውንዴሽኑ ከአሁን እስከ ዲሴምበር 2 ድረስ ስለ "Dine with Dignity" ለማስተዋወቅ በ Starbucks ድጋፍ **የቡና ጠረጴዛዎች ላይ** እና **የቁርስ ቦታዎች** በ46 የሞንትጎመሪ ካውንቲ Starbucks ሥፍራዎች ዘመቻ ይካሄዳል። የበለጠ ለመማር እና ዛሬ እርዳታ ለመስጠት ይህንን ድረ-ገጽ ይጎብኙ፡-www.mcpsfoundation.org/dine206.

**ስለ Parent Portal የእርስዎን ሃሳብ ያካፍሉን**

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አዲስ የተማሪዎች መረጃ/ኢንፎርሜሽን መዋቅር/ሲስተም ለመዘርጋት ፕሮፖዛል(RFP) እየሠጠ ነው። መዋቅሩ/ሲስተሙ አዲስ parent/student portal ይጨምራል። ዲስትሪክቱ ስለ "online parent portal" አጠቃቀም ሁኔታ የወላጆችን አስተያየት ለመስማት ይፈልጋል፣ በተጨማሪም

- አካውንት ስለመክፈት እና አጠቃቀም/አያያዝ
- የጊዜ ሰሌዳ/መርኃ ግብር፣ ውጤቶች/የክፍል ደረጃ፣ የትምህርት ክትትል እና ለፈተና ውጤቶች መድረስ/መዳረሻ
- በትምህርት ቤት/በመምህር የተለጠፈ ይዘት መዳረሻ
- ጠቃሚ/አስፈላጊ ቅጾችን በአውታረ-መረብ ላይ ለመሙላት መቻል
- ሞባይል ወይም የሞባይ app ምርጫ

ዳሰሳውን ይሙሉ

**አዲስ ሚስጥራዊ የሆነ የመጠቆሚያ መስመር አለልዎ**

"Safe Schools Maryland Tip Line" ማለት ምስጢሩ የተጠበቀ ሪፖርት ማድረጊያ ሲስተም ሲሆን በዚህ ሲስተም በመጠቀም ስለተማሪዎች አስጊ ሁኔታዎችን እና/ወይም ደህንነት ስጋቶችን ሪፖርት ማድረግ ይቻላል።

በጠቅላላ በሜሪላንድ የሚገኙ ተማሪዎች፣ ወላጆች/ሞግዚቶች፣ ፋኩልቲ፣ ሠራተኞች፣ እና የማህበረሰብ አባላት ይህንን ሚስጥሩ የተጠበቀ አፕሊኬሽን እና የድረ-ገጽ ሲስተም/app and web-based reporting system/በመጠቀም የሚከተሉትን የሙሣሡሉ ስጋቶቻቸውን ለማካፈል ይችላሉ፡-

- የአእምሮ ጤንነት ቀውስ
- በጉልበተኝነት ማጥቃት
- የትምህርት ቤት እና የማህበረሰብ ግጭት/ሁከት
- የእፅ/የመድኃኒት እንቅስቃሴ
- ማንሳቀል፣ መጉዳት፣ ስድብ፣ ጥቃት፣ እንግልት
- ወከባ
- በሜሪላንድ ተማሪዎች ላይ ተጽእኖ የሚያደርጉ ሌሎች ጉዳዮች

የ "Safe Schools Maryland Tip Line" መስመር ጉዳት የሚያስከትሉ ሁኔታዎችን በቀዳሚነት ለመከላከል ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች የሚያገለግል መሣሪያ ነው። "The Safe Schools Maryland Tip Line" የሜሪላንድ

ዜጎችን/ነዋሪዎችን ስለ ትምህርት ቤቶች እና የተማሪዎች ደህንነት የመጠበቅ/የመከላከል ዝግጁነት ባህል እንዲያዳብሩ እና የተለያዩ ዓይነት የመገናኛ ዘይቤዎችን በመጠቀም ሪፖርት ማድረጊያ እና ማስተላለፊያ የሚያግዝ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ ያለዎትን ስጋት ለመግለጽ እና app ለማውረድ/ለመጫን ይህንን ድረ-ገጽ ይጎብኙ፡- safeschoolsmd.org/.

**የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሥራ ማስኬጃ ባጀት ለማዘጋጀት እንዲረዳዉ የእርስዎን አስተያየት ይፈልጋል**

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ለበጀት ዓመት 2020 የሥራ ማስኬጃ ባጀት ዲስትሪክቱ ማተኮር ያለባቸውን አቅጣጫዎች ልዩ/ግልጽ አስተያየቶችን ለማግኘት ይፈልጋል። ለሁሉም ተማሪዎች ውጤቶችን ለማሻሻል ለማገዝ የትኞቹ ስልቶች/ስትራተጂዎች፣ ፕሮግራሞች ወይም ጥረቶች ጠቃሚ መሆናቸውን ወይም የማይጠቅሙ መሆናቸውን ይንገሩን።

እባክዎ የእርስዎን ግብረመልስ ለመስጠት ይህንን አጭር ዳሰሳ ይሙሉ። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ከዚህ ዳሰሳ የሚገኘውን መረጃ/ኢንፎርሜሽን የሚዘጋጀውን ባጀት ለማዳበር ይጠቀማል።